# የመለስ ... ጉዞ “ሸውራራ ብትኳል ለትዝብት”

ከአረጋዊ በርሀ

በቅርቡ **“መለስ ዜናዊ እና የህወሓት የትግል ጉዞ ”** በሚል ርእስ፣ ፀሓፊ ኢያሱ መንገሻ (ኮ/ል) ተብሎ፣ ባለ 313 ገፆች ኣንድ መፅሓፍ መጋቢት 2002 ዓ.ም. ኣዲስ ኣበባ ታትሞ ወጥቶ፤ ከጫፍ እስከ ጫፍ ኣነበብኩላቸው። መፅሓፉ ኣቶ መለስን ልዩ የታሪክ ካባ ለማልበስ ሲባል ብዙ የተደከመበት የፈጠራ ቅንብር መሆኑ ገና ከሽፋኑና ከመቅድሙ ያስታውቃል። ለዚሁም በተጨማሪ ፕሬዚደንት ግርማ ወ/ጊዮርጊስ ከባህል ሚኒስትሩ ጋር በመሆን በሸራተን ሆቴል ደግሰው 22 ነሓሴ 2002 ዓ/ም መርቀውለታል። ፀሓፊው ኮ/ል ኢያሱ መንገሻ ይባል እንጂ በዚህ የፈጠራ ቅንብር የኣቶ መለስ እጅ በእጅጉ እንዳለበት ብዙ ጠቋሚ ነጥቦች በዚህ መፅሓፍ ይገኛሉ። ለመለስ ቅርበት ኣለኝ የሚለው ኮ/ል ኢያሱ፣ ቅርበቱ እዚህ ላይ እንዴት እንደተጠቀመበት ባይገልፅም ቅንብሩ ራሱ ይመሰክርለታል። ከዚህ ኣልፎም ኣንዳንድ የቅርብ ታዛቢዎች ‘መለስ ራሱ የፃፈው ድርሰት ነው’ ሲሉ ይደመጣሉ። ትዝብቱ ልክ ሊሆን ይችላል ምክንያቱም የኣቶ መለስ የሙጉት ዘይቤ በመፅሓፉ በስፋት ከመታየቱ ባሻገር ሰውየው ድምፁን እየቀለባበሰ “ፓል-ቶክ” ውስጥም ጭምር ገብቶ ኣራዳዊ ክርክሩን በመርጨት የሚታወቅ ነውና። እንግዲህ ቀጥሎ በዚህ መፅሓፍ ላይ ያለኝን ኣጠቃላይ ትዝብት ሳቀርብ፣ ትችቱ ኣቶ መለስን እና ”ፀሓፊው” ኮ/ል ኢያሱን የሚመለከት ሆኖ ድርሰቱ ዋና ዓላማ ኣድርጎ በያዘው ‘የመለስ ጉዞ በህወሓት’ እና እኔም በቀጥታ በማውቃቸው ኣቶ መለስን በተመለከቱ ጉዳዮች ላይ ብቻ ያተኩራል። በዚህ መልክ የመፅሓፉ ኣጠቃላይ ገፅታ ለመገንዘብ የሚከብድ ኣይሆንም።

**“ ሸውራራ ብትኳል ለትዝብት”** የሚል ኣባባል ከትግርኛው “ሓባልስያ መጠመቲኣ ትኳሓል” የሚለው የተተረጎመ ሆኖ፣ ኣንድ ሰው እራሱን ባልሆነ ታሪክ የሚቀባ ከሆነ ትኩረትን ይስባል - በሂደቱም ጉዱ ይታያል ወይም ቅባቱ ሲረግፍ ውስጣዊው መልኩ ኮለል ብሎ እንዲወጣ ይጋብዛል ለማለት ነው። በዚሁ መፅሓፍም የሆነው ይኸው ግብዣ ነው፣ የራሱን ገበና እንዲጋለጥ በሚገፋፉ መልኩ ቀርበዋል። ስለሆነም የፈጠራ ታሪክ በሓቀኛ ታሪክ ተመስሎ ለትውልድ መተላለፍ የለበትም ከሚል እምነቴ በመነሳት በውሸት የተቀነባበረው ትረካን በመጣል ሃቁን ለማስቀመጥ እጥራለሁ። ኣቶ መለስና ኮ/ል ኢያሱ ሊፈጥሩት ባቀዱት ኣዲስ ታሪክና በቆለሉት የማዘናጋት ስራ እኔም ሆነ ሌሎች በወቅቱ የነበሩ ታጋዮች የምናውቀው ታሪክ ግልፅ ኣድርጎ በማስቀመጥ ሃቁን ማካፈል ተገቢም ግዴታም ይመስለኛል። በእውነቱ ነገሩ በኣጠቃላይ ሲታይ ስለ ኣቶ መለስ ጉዳይ ሊመስል ይችላል። ኣይደለም። ዋና ቁምነገሩ ትውልድ የደፈረሰ ወይስ የጠራ ታሪክ ስለመቅሰሙ ጉዳይ ነው።

ኣምና (2001) በዚህ ወቅት “ፅንዓት” የተባለ ስለ ኣቶ ስዩም መስፍን ኣንድ መፅሓፍ መታተሙ ይታወሳል። ዓላማውም ስዩምን ማወደስ ሆኖ ታሪክን በማዛባቱ በኩል ከዚህኛው ድርሰት ኣይለይም። በዛው ወቅት “ኣጉል ሙገሳ ወይስ እውነተኛ ታሪክ ?” በሚል ርእስ ስለ መወድሱ ትችቴ ሳቀርብ ያኛው መፅሓፍ ኣሁን ለምተችበት የኣቶ መለስ መፅሓፍ ኣሳሽ (መፈተኛ) መሆኑ ጠቁሜ ነበር። እጠቅሳለሁ፣

**“ለገሰ (መለስ) ደግሞ ከስዩም በላይ የታሪክ ቅባት የሚያስፈልገው ፍጡር ነው፡፡ ከዚህ መፅሓፍ መውጣት ቀደም ብሎ “ኢትዮጵያን ያለ መለስ ማሰብ አይቻልም” የሚል መፈክር ማየታችን አንረሳውም፡፡ በዚህ ምክንያት ‘እውነተኛ ታሪክ’ እየተባለ ውዳሴ መፃፍ የተጀመረበት ምስጢር የት ሊያደርሰን እንደታለመ አስቀድሞ ማወቁ የግድ አስፈላጊ ነው፡፡ ስለዚህ ዋናው የ’ፅናት’ ዓላማ የለገሰ ዜናዊ አዲስ ታሪክ ለመፃፍ አመቺ ሁኔታ መፍጠር እንደሆነ መገንዘብ ያስፈልጋል፡፡ በዚህ የስዩም ተረት-ተረት መቅመሻ የሚሆን ስራ ተጀምሯል፡፡ የስዩም ውዳሴ (ፅናት) ተከትሎ ለሚመጣው የለገሰ ውዳሴ መሞከሪያ ነው፡፡”**

ይኸው ይህ በተባለ በኣመቱ የለገሰ ዜናዊ ኣዲስ ታሪክ (የኣቶ መለስ መወድስ) ለማየት ደረስን። ይሁን እንጂ መፅሓፉ ጭንቀት ኣዝሎ ነው ብቅ ያለው።ፀሓፊው ኮ/ል ኢያሱ መንገሻ ምን እንዳስጨነቀው ራሱ ይነግረን ይሆን እንጂ ከመፅሓፉ ውስጥ (ገፅ 23) ና በሽፋኑ ላይ በድጋሚ የሚጠቀሳት ኑዛዜ መሳይ ጥቅስ ኣለችው። እንዲህ ይላል “እኔ የማምነውና ራሴን የምመለከተው ትላንትም ሆነ ዛሬ ከህሊናዬና ከእምነቴ ጋር እንጂ፣ ከሌላ ጋር የለሁም ብዬ ነው። ሆኖም ይህን ስራዬን በተመለከተ ከፊቴም ሆነ ከጀርባዬ ሰው እንዲኖር ኣልሻም። የኔ መነሻና ጉዳይ ከታሪክ ጋር እንጂ ከሰዎች ጋር ኣይደለም። ታሪካችንን በትክክልና በነበረው መንገድ መግለፅ መቻል ኣለብን ብዬ ኣምናለሁ። ምክንያቱም ሰዎች ለታሪክ ነው የተፈጠርነው። ለታሪክ ነው የምንኖረው። አስነዋሪው ነገር ለታሪክ መኖር ሳይሆን በታሪክ መኖር ነው።” (ሰረዝ የተጨመረ)። በታሪክ መኖር የሚፈልገው ታድያ ማን ይሆን? ለዛውም በፈጠራ ታሪክ!

ኮ/ል ኢያሱ ከህሊናዬና ከእምነቴ ጋር እንጂ፣ ከሌላ ጋር የለሁም ሲለን መቸም ያለምክንያት ሊሆን ኣይችልም። ይህ ለማለት ያስገደደው ነገር ቢያንስ ካቶ መለስ ጋር ሸርጉድ ሲል የታዘቡትን ሰዎች ለማየት ኣሳፍሮት ነው፣ ኣለዚያማ ከመለስ ጋር በቅርበት መኖሩ በቀላሉ ከፅሑፉ ሊደረስበት ይቻላል። ቅርበቱ እሱም ኣልካደም። ቀጥሎ ግን ከፊቴም ሆነ ከጀርባዬ ሰው እንዲኖር ኣልሻም ይላል። መጀመርያ ከሌላ ጋር የለሁም ብሎ ኣረፈው ስንል ወዲያው ደግሞ ከጀርባው ሰው ላይኖር እንደሚሻ ይነግረናል። ምን ኣስለፈለፈው ? “የኣባ ገሪማ ‘መባእ’ የቀመሰ ሳይጠየቅ ይለፋለፋል” ብለን እንለፈውና ስለ “ትክክለኛ ታሪክ ፀሓፊነቱ” ከሚጠቅሰው እንመልከት።

ገና ከመፅሓፉ መቅድም ገፅ-II ላይ ሁለት ኣስገራሚ የመለስ ዜናዊ ጥቅሶች ብሎ ይደረድራል። ሁለቱም ተመሳሳይነት ቢኖራቸው እንያቸው፣ **“እኔ እንደ ኣንድ ትልቅ ነገር ኣድርጌ የምወስደው ሰዎች በፍርሃት ወደ ሁዋላቸው ሳይገላመጡ በነፃነት ሊናገሩ የሚችሉ መሆናቸውን ነው።”** (ግንቦት 1991)
**“ዴሞክራሲ ማለት ዜጎች ሓሳባቸውን በነፃነት እንዲገልፁ መፍቀድ ሲሆን፣ በሌላ በኩል ዜጎች ሓሳባቸው በነፃነት እንዳይገልፁ በሌሎች የሚደረግባቸው ጫና ካለባቸው ግን ይህ ድርጊት ኢ-ዴሞክራሲያዊ ይሆናል።”** (ቀን ኣልባ)

እነዚህ 2 የኣቶ መለስ ዜናዊ ጥቅሶች በመቅድሙ የደረደረ ፀሃፊ ትክክለኛ ታሪክ በማለት ስለ ኣቶ መለስ ምን ሊተርክ እንደፈለገ ለማወቅ ወደ መፅሓፉ ዘልቆ መግባትም ኣያስፈልግም። ባጭሩ ከግንቦት 1991 ኣንስቶ የመለስ ዜናዊ እምነት ሰዎች ያለ ፍርሃት ሓሳባቸው በነፃነት መግለፅ እንዳለባቸውና ጫና ካለባቸው ግን ይህ ድርጊት ፀረ-ዴሞክራሲያዊ መሆኑ ሊያስረዳን መፈለጉን ያሳያል። እንግዲህ 'ጭሆቴን ቀሙኝ' የሚያሰኘው የፈጠራ ትረካው፣ ከዚሁ ከሓቁ ጋር ፊት ለፊት ከሚጋጨው ጥቅስ ይጀምራል።

በኣፋኝነቱ፣ በፀረ-ዴሞክራሲና በኣረመኔያዊ ተግባሩ የኢትዮጵያ ህዝብ ብቻ ሳይሆን ዓለም ያወቀውና ያወገዘው እንዲያውም ለፍርድ መቅረብ ኣለበት የተባለውን ሰው የሓሳብ መግለፅ ነፃነትና የዴሞክራሲ ኣራማጅ ኣድርጎ ማቅረብ ምንኛ 'ኣራምባና ቆቦ እንደመታ'ና ፍፁም ሓላፊነት የጎደለው ኣድርባይነት መሆኑ ልብ እንበል። ምናልባት ፀሓፊው ባንድ በኩል 'ጠቅላይ ሚኒስትር' መለስን ኣስመልክቶ በዓለም ዙርያ ምን እየተባለ እንደሆነ የማይከታተል የመለስ ጭፍን ኣምላኪ፣ በሌላ በኩል ደግሞ በኣዲስ ኣበባ ብቻ ብዙ ህዝብ በጭካኔ እንደተጨፈጨፈ፣ እንደተጠለፈና እንደታፈነ እያወቀ እንዳላወቀ ሆኖ የሚቀርብ የቤተ-መንግስት ፀሓፊ ሊሆን ይችላል። ለአብነት በየወቅቱ (1983፣ 1987፣ 1997) በጭካኔ የተገደሉት ኣያሌ የኣዲስ ኣበባ ዩንቨርሲቲ ተማሪዎች፣ በምርጫ 97 ያለቁት 193 ንፁሃን ዜጎች ሊደብቀን ይከጅለው ይሆን? በ1998 ለተፈጁት 424 የጋምቤላ ኣኝዋክ ወገኖቻችንስ ረስቷቸው ይሆን ? በኣዋሳ የፈሰሰው የሰላማዊ ህዝብ ደም ማን ሊጠየቅበት ነው ?

ክስተቱ ኣዲስ ነገር ኣይደለም። ድሮውም እኮ "የቤተ-መንግስት ፀሓፊ" (palace author) የሚባል ኣልጠፋም፣ የኣሁኑ ቅጥ ኣጣ እንጂ። በተለይ የፀሓፊው ማስታወሻ በሚለው መቅድሙ (ገፅ III) "መለስ ማን ነው ?" ብሎ እራሱ ጥያቄ ይቀሰቅስና መልሱ ደግሞ እራሱ በገፅ IV ሲሰጥ "መለስ ትልቅና የተከበረ የሃገራችን መሪ መሆኑ ይታወቃል" ይላል። 'የኣይጥ ምስክሯ ድንቢጥ' ይባል የለ! ወረድ ብሎም ያንን ኣባባሉ ሰዉ ዓይኑን ጨፍኖ እንዲቀበልለት ስለፈለገ ይመስላል "ህወሓት ማለት የተለዩ ግለሰቦች ወይም ሰዎች ናቸው ብዬ ኣላምንም። እኔ ነኝ ብዬ ነው የማምነው።" በማለት ድንፋታ መሳይ በመልቀቅ በዛው እንዲታመን ይጥራል። ለመሆኑ ህወሓት እንደ ድርጅት ኣሁን ኣለ እንዴ ? ኣቶ መለስ ህወሓትን እንደካደ፣ በተቀሰቀሰው ግርግር ኣብዛኛው ፖሊት ቢሮና ማእከላይ ኮሚቴ ሲባረር ድርጅቱ እንዳበቃለትና በኣንድ ሰው ኣምባገነንነት እንደተተካ ገና ኣልገባው ይሆናል ። ለፖለቲካ ጨዋታ ያመች እንደሆነ እንጂ ኣሁን ህወሓት ብሎ ድርጅት ሊኖር ኣይችልም። ከዚሁ 2 ገፆች ቀደም ብሎም "ምስጋና" ብሎ ርእስ ይሰጥና ያንድም ሰው ስም ሳይጠቅስ በደፈናው "ለሁሉም ምስጋናዬን ኣቀርባለሁ" ይላል። ለምን ? ተባባሪ ያለቅጥ ስለ በዛና መዘርዘሩ ስላልቻለው ? ወይስ በኣንፃሩ መለስና እራሱ ብቻ ተደብቀው የሰሩት ድርሰት በመሆኑና ሌላ ተባባሪ መጥቀስ ስለማይቻል ? መልሱ ቀስ ብለን እንደርስበት ኣለን።

ወደ ዋናው የመፅሓፉ ይዘት ስንገባ እያንዳንዱ የፈጠራው ታሪክ ነጥብ-በነጥብ ለቅሞ ለመተቸት ሲታሰብ በእውነት ጊዜና ቦታ ኣይበቃም። ያለቅጥ የተንዛዛ ፈጠራ ነው። በተጨማሪም የታሪኩ ጊዜ ሩቅ ስላልሆነና ትግሉን በቅርበት የሚያውቁ በርካታ ታጋዮች በህይወት ስለሚገኙ፣ ሁሉም በቅርበት በሚያውቀው ላይ ይተችበታል ከሚል እምነት፣ የኔ ብዙ መድከም ኣያስፈልግም። ስለዚህ እኔ በቅርበት የማውቃቸውና ቢገለጡ ይጠቅማሉ በምላቸው የተወሰኑ ፈጠራዎች (ውሸቶች) ላይ ብቻ በማተኮር የመፅሓፉን ኣጠቃላይ ይዘትና ዓላማ ለማብራራት እሞክራለሁ። የመፅሓፉ ዋናው ዓላማ ኣቶ መለስን "ትልቅ ሰው" ኣድርጎ ለማቅረብ ነው፣ ስለሆነ የትግል መስራችም ያደርገዋል።

**ስለ "መስራች" መባል**

በመጀመርያ ፀሓፊው በገፅ IV "መለስ ትልቅና የተከበረ የሃገራችን መሪ መሆኑ ይታወቃል" ለሚለው "ጠ/ሚ" መለስ የህወሓት ነባር ኣባል ማለቱን ስላነሰው ይመስላል መስራች ኣባል ኣድርጎ ለማቅረብ  የሚጠነጥነው ሙግትና የሚጠፈጥፈው ስእል በጣም ኣስገራሚ ነው። **ቀንና ቦታ** ጠቅሶ መለስ መስራች "ነው" ወይም "ኣይደለም" ብሎ ባጭሩ ማለፍ ሲቻል፣ መስራች መባሉ ትልቅነትን የሚያስገኝ ስለመሰለው ይሆናል በዚህ ላይ በመደጋገም በጣም ብዙ ገፆች ኣባክነዋል። ቀንጨብ ኣርጎ ለማሳየት ያህል ለምሳሌ በገፅ 23 "**ከእነዚያ መስራቶች መካከልም መለስ ዜናዊ ኣንዱ ነበር።**" ይልና ቀጥሎም "**መለስ የትጥቅ ትግልን ከጀመሩት 11 ኣባላት ኣንዱ የነበረ ባይሆንም ... ህወሓትን የመሰረተው ማገብት ኣባላት ከነበሩት ኣንዱ ግን ነበር። ሆኖም ህወሓትን በመጠንሰሱም ሆነ በመጥመቁም ተግባር ከነበሩትና ከተሳተፉት መስራቶች ኣንዱ ነው ብሎ ኣፍን ሞልቶ መናገር ይቻላል።**" እያለ እርስበርሱ የተምታታ ክርክር በማቅረብ ወደ ገፅ 24 ይሻገርና፣ "ወደ ትግሉ ዘግይተው ከተቀላቀሉት መካከል በተለይ ኣቶ ስብሓት ነጋና ኣቶ መለስ ዜናዊ ..." በማለት ኣረጋዊ በርሀ በጦብያ ቅፅ4 ቁ11 89 ዓ/ም የገለፀውን "ታሪክን ጠቅልሎ የመውሰድ እንደምታ" ነው ብሎ ያማርራል/ሉ። እንዲህ ከማላዘን ይልቅ ከስብሓትና ከመለስ ጋር ፊት-ለፊት ቃለ-ምልልስ በማካሄድ "**መቼ ? የት ቦታ ?** ትግሉን ተቀላቀላችሁ ብሎ በመጠየቅ የሚሉትን እቅጩን መስማት ኣይቀልም። ለምን ይሆን ታዲያ ስለዚህ ጉዳይ ከነሱ ኣፍ የማያዳምጠው? እና ከ313 ገፆቹ በኣንዷት መስመር ላይ የማይፅፈው ? 'ደሮ ጭራ የምታገኘው ዘዴ' እንዲሉ፣ በነሱ ኣፍ መነገሩ የተፈራው ውሸት ለኢያሱ በማቀበል ቀለም ተላብሶ እየተረጨ ነው። **ግራም ነፈሰ ቀኝ መለስና ስብሓት ማገብትን ይሁን ተሓህትን/ህወሓትን ኣልመሰረቱም፡ እንዳውም ሁለቱም ትጥቅ ትግሉን የተቀላቀሉት ከወራት በሁዋላ ነው** 4 ነጥብ

ስትራቴጂያችን ዴሞክራሲያዊት ኢትዮጵያ፣ ስልታችን ብሄራዊ ትግል በማለት ኣዲስ ኣበባ ውስጥ ፕሮግራም ነድፈው፣ መጀመርያ ማገብት በሁዋላ ተሓህት/ህወሓት የተሰኘው ድርጅት መስርተው ትጥቅ ትግሉን የጀመሩ/ያስጀመሩት ታጋዮች 1/ስሑል፣ 2/ኣግኣዚ፣ 3/ግደይ፣ 4/ስዩም፣ 5/ኣባይ፣ 6/ሃይሉ፣ 7/ኣስፍሃ 8/በሪሁ ናቸው። ይህ ሲባል ከነዚህ መስራቾች ያላነሰ **ቆራጥ** ኣስተዋፅኦ ያደረጉ በርካታ ቀደምት ታጋዮችም ኣልነበሩም ማለት ኣይደለም። እነ ቀለበት፣ ካሕሳይ፣ ብርሃነ፣ ኣስገደ በደደቢት በኩል - እነ ዋልታ፣ ሸዊት፣ ስየ፣ ኣውዓሎም በኤርትራ በኩል ተሰማርተው ትልቅ ኣስተዋፅኦ ማድረጋቸው የታወቀ ነው። መለስ ግን እንኳን መስራች ሊሆን በዚህኛውም ሊካተት እንደማይችልም መታወቅ ኣለበት 4 ነጥብ

ነገር ነገርን ያነሳዋልና፣ ይልቅ የመስራችነቱ ፈጠራ ትተን ኣቶ መለስ ዜናዊ ለስልጠና ወደ ኤርትራ ሲጓዙ ከነበሩት ጓዶቹ ለብቻው ተነጥሎ ኣስመራ ላይ ሌሎቹ ሳያውቁ የተሰወረባቸው ምክንያትና የት-የት እንደሰነባበተ፣ እንደዚሁም እንደገና ተሓህትን ለመቀላቀል ሽራሮ በተባለው ቦታ **ኣመልክቶ** ስለመፈቀዱ ኮ/ል ኢያሱ ቃለ-መጠይቅ ኣካሂዶ መልሱን ከራሱ ከመለስ ዜናዊ እንድንሰማው ቢያደርግስ? ይህ ስል በየስብሰባውና በየቃለ-ምልልሱ ህዝቡ እንደሚታዘበው ኣራዳዊ መልስ ኣያጋጥምም ማለት ኣይደለም። እውነታውና የሰውየው ባህርያት ሲጋጩ ማየቱ ግን የምንታዘበው ነገር ኣይጠፋም ከሚል ነው እንጂ።

በገፅ 37 “መሰወር ፈልጎ ስለተሰወረ ኣልነበረም” ለሚለው የትም የማያደርስ ሙግት ‘ምን ፈልጎ ነው ታዲያ (የተሰወረውን ትተን) የጠፋው?’ ብንልስ መልሱ ምንድን ነው። ለ35 ዓመታት በኣቶ መለስ ኣንገት ላይ የተንጠለጠለው ጥያቄ እስከ ኣሁን የረባ መልስ ኣላገኘም። መቸም ባህታዊ ለመሆን ፈልጎ እንዳልተሰወረ ክስተቱ ኣብራርቶታል። የተሰወረበት ወይም የጠፋበት **<u>ዋናው ምክንያት</u>** ከራሱ እስከንሰማው ድረስ ጥያቄው እንደተደገነ ይቆያል፣ ያም ሆኖ ‘ፍርሃት’ ወይም ‘ከኤርትራው ግንባር በድብቅ ለመገናኘት’ የሚሉ መልሶች ባንጠብቅ ደግ ነው።

እዚህ ላይ ብዙም የማያከራክሩ 2 ነጥቦች ኣስቀምጦ ማለፍ ይቻላል። 1ኛ/ መስራች ወይም መስራቾች ማለት ለተወሰነ ዓላማ ግብ መምታት ኣንድን ድርጅት፣ ማሕበር፣ ተቋም፣ ወዘተ የሚያቋቁም/ሙ ሰው/ሰዎች ማለት ነው። የድርጅቱ መመስረቻ **ጊዜና ቦታ** ደግሞ ተጨባጭ በሆነ መንገድ መታወቁ የግድ ይላል። ከጊዜና ቦታ ውጭ የሚሆን ነገር የለምና። በዚህ ኣድማሳዊ ስሌት መለስ መግብያ የለውም። 2ኛ/ በዛ ጠመዝማዛ ኣራዳዊ ክርክሩ ኣቶ መለስ “እኔ መስራች ነኝ ኣላልኩም፣ ኢያሱ ነው እንጂ የለቀለቀው” ሲል ይጠበቃል። ለዚህም ነው ራሱ የሚፈጥራቸው ሃገር-ኣጥፊ ፖሊሲዎችና ውሳኔዎች የፓርላማ ወይም የሚኒስትሮች ምክር-ቤት ውሳኔ እያስመሰለ ተግባር ላይ የሚያውለው። ነገ ኣይቀሬው ተጠያቂነት መምጣቱ ስላላጣው መከላከያ ማበጀቱ ነው። ዓላማው ፓርላማውና ሚኒስትሮች ምክር-ቤቱ ኣብረዉት ተጠያቂ ለማድረግ ቢሆንም ከዋና ተጠያቂነት ግን ኣያድኑትም። ለነገሩ ሁለቱም የሱ ኣጃቢ መሆናቸው ቢታወቁም ለኣጥፊ ውሳኔዎቹ ከተጠያቂነት ያመልጣሉ ማለትም ኣይደለም። የሆነ ሆኖም የፈጠራ ታሪኩ ኮ/ል ኢያሱ ቢለቀልቀው ቅሉ ነገ ቀኑ ሲደርስ “ኣስተባበልክ ወይ” ለሚለው ጥያቄ እንዴት ይመልሰው ይሆን ?

**ስለ መገንጠል ዓላማ**

መፅሓፉ ከገፅ 84 ጀምሮ የመገንጠልን ጥያቄ ኣንስቶ መለስን ከፈፀመው ጥፋቱ ለማዳን የተለመደው ኣራዳዊ ክርክሩን ይዘከዝካል። ትግራይን የመገንጠል ዓላማ በማኒፌስቶ-68 ተፅፎ ስለወጣ በኣራዳዊ ክርክር ለመክዳት ወይም ኣምታቶ ለማስተባበል የማይሞከር ነው። ተጠያቂው ማን ነው ? ለሚለው ግን ብዙ ኣልባሌ መልሶች እየቀረቡ ቢሆኑም፣ የመገንጠል ጥያቄ ማን ኣነሳው ? ማን ፃፈው ? መቼ ? የት? ብለን ከጠየቅን መልሱ በቀላሉ የሚገኝ ነው።

መቸም በነዛ ‘ኣብዮታዊ’ ኣመታት “የብሄሮች የራስን ዕድል በራስ የመወሰን እስከ መገንጠል መብት” ብሎ ያልተነሳ ‘ኣብዮታዊ’ ኣልነበረምና ተሓህትም ከዚሁ ልቅ ኣባዜ ኣላመለጠም ነበር። ይሁን እንጂ መገንጠልን እንደ ዓላማ ኣድርጎ የሚንቀሳቀስበት ድርጅት ሆኖ ኣልጀመረም። ቀደም ሲል እንደተጠቀሰው <u>ስትራቴጂያችን ዴሞክራሲያዊት ኢትዮጵያ፣ ስልታችን ብሄራዊ ትግል</u> የሚል መምርያ ኣንግቦ ደደቢት ከተወረደ በሁዋላ ኣቶ መለስና ኣቶ ስብሓት እስኪቀላቀሉ ድረስ የመገንጠል ጥያቄ ያነሳ ታጋይ ኣልነበረም። ለመጀመርያ ጊዜ ሰኔ ወር 67 ዓ/ም ሕርሚ በተባለው ቦታ የትግራይን የመገንጠል ጥያቄ ያነሳው ኣቶ ስብሓት ሲሆን፣ “ታሪካዊና ፖለቲካዊ ጭብጥ ኣቅርብለት” ተብሎ ስለተያዘና ማቅረብ ስላልቻለ ኣባባሉን ለጊዜው ውጦት ቀረ። ሆኖም ግን ያኔ ብዙም ከማይታወቀው መለስ ጋር ኣብረው ተባብረው በህቡእ ከይሲ ስራቸውን ተያያዙት።

በ68 ዓ/ም የተሓህት ፕሮግራም ዘርዘር ተደርጎ እንዲቀርብ ሲወሰን መለስ ዜናዊ ከኣርቃቂዎቹ ኣንዱ በመሆን ተመደበ። ኣጋጣሚውን በመጠቀም፣ መገንጠልን እንደ ዓላማ የያዘ ፕሮግራም በጥድፍያ ኣረቀቁ። ረቂቁ ኣመራሩ እንደገና ሳይመለከተው ለሕትመት ወደ ሱዳን በኣቶ ስዩም በኩል ተላከ። ኣቶ ስዩም ፅፎ ኣሳተመው። የታተመው ቅጅ ሜዳ ደርሶ ገልጠን ስናየው “የትግራይ ነፃ ሪፓብሊክ መመስረት” (መገንጠል) ይላል። ወድያው የተበተኑት ቅጂዎች እንዲሰበሰቡና መገንጠልን ዓላማ ያላደረገ “ የራስን ዕድል በራስ የመወሰን መብትን በዴሞክራሲያዊት ኢትዮጵያ ጥላ ስር ማስከበር” በሚል እንዲተካ ተወሰነ፣ ተደረገም። እንዲህ ይወሰን እንጂ የመገንጠሉ ኣባዜ ከነመለስ/ስብሓት ራስ ተፍቆ ወጥተዋል ማለት ግን ኣልነበረም። ኣሁንም ኣይደለም። ኣንዱ የልዩነታችን መንስኤም ከዚሁ ውስጠ ነገር የመነጨ ችግር መሆኑ ከወዲሁ ስገልፅ፣ የዚህ ስውር ደባ ዝርዝር ሂደት በወቅቱ በጉባኤ ቀርቦ ተጠያቂዎቹ ሁሉም ታጋይ እንዲያውቃቸው ኣለመደረጉ ትልቅ ጥፋት እንደሆነ ጠቅሸ ማለፍ እወዳለሁ።

**ሙልጭ ያለ ቅጥፈት**

ፈሪን ጀግና ኣድርጎ ለማቅረብ ‘በዚህ-ቢሉት-በዚያ’ የሚሆን ነገር ኣይደለም። ፈሪ መሪ ደግሞ ኣስፈራርቶ መኖር ብቻ ስለሚያውቅ ኣይደበቅለትም። ግን በመፅሓፉ ገፅ 120 ላይሳካ ተሞኩረዋል። ፀሓፊው ኮ/ል ኢያሱ በዛ ፍርሃት በተከሰተበት ኣካባቢ ስላልነበረ ስለሁኔታው ከኣቶ መለስ ሊያገኘው ካልሆነ በስተቀር የሚያውቀው ነገር የለውም። ሙግቱም ያው የተለመደው የመለስ የማምታታት ዘይቤ መሆኑ ይታያል፣ እንዲህም ይላል፣ “…ቆፃሎ በተባለ ቦታ የተካሄደውን የ92ኛ ሻምበል የግምገማና የማጣራት መድረክንና እንቅስቃሴን የመሩት ኣረጋዊ በርሀና መለስ ነበሩ። …ዴምክራሲያዊ ኣቀራረብና ኣካሄድ በመከተል መለስ ኣዎንታዊ ሚና እንደተጫወተም ይነገርለታል።” ይህ ገለፃ ከፈጠራ ያለፈ ነጭ ውሸት ቢባል ኣግባብነት ኣለው። ምክንያቱም በተባለው ቦታ የ92ኛ ሻምበል ስብሰባ የተጠራበት ምክንያት መለስ ከዚች ኣሃድ (unit) ጋር በመሆን የዓድዋ ፖሊስ ጣብያ እንዲያጠቃ ተመድቦ ሲያበቃ ከውጊያ መስመሩ ስለሸሸና ውጊያው በመበላሸቱ ግለ-ሂስ እንዲውጥ ኣልያም እንዲነቀፍ ነው። እየተገለባበጠ በረጅም ግምገማ ኣልፎ

ጥፋቱን ስለ ኣመነ ወታደራዊ ቅጣት ተወስኖበት ቅጣቱንም ኣግኝተዋል። ታድያ እንዴት ሆኖ ነው ተከሶ ለምርመራ የቀረበ ሰው የስብሰባ መሪ፣ ያውም ኣዎንታዊ ሚና ተጫዋች የሚሆነው። ቅጥፈት ይሉታል እንደዚህ ነው።

በገፅ 138 ደግሞ የባሰውን እናያለን። "...ነሓሴ 21 1969 ዓ/ም ዓዲዳዕሮ... በዚህ ውጊያ የመቁሰል ኣደጋ ከደረሰባቸው ታጋዮች መካከል መለስ ኣንዱ ነበር።" ይላል። ይህ ውጊያ እኔው ራሴ እመራው ነበርኩኝ፣ ውግያው ተፈፅሞ መለስንም ኣግኝቸው ነበር። የጭንቀት ካልሆነ በስተቀር የመቁሰል ኣደጋ ይቅርና ትንሽ ጭረትም ፈፅሞ ኣልደረሰበትም። ይኸው ውሸት ኮ/ል ኢያሱ ሊፈጥረው ኣይችልም። የሚገርመው ይህን ፈጠራ ኣስመልክቶ ኣቶ መለስ በጋዜጣም ካንዴ-ሁለቴ ኣስተጋብቶታል። ይህ ደግሞ ሙልጭ ያለ ቅጥፈት ነው።

በዚህ ሳያበቃ፣ በገፅ 242-3 "... ይጓዙ የነበሩት <u>በመለስ ኣገላለፅ</u> በፈንጂ ወረዳ ውስጥ ነበር" ይልና ከዛው ከበባ መለስ በጀግንነት እንዴት እንዳመለጠ ይዘረዝራል። ይህ ደግሞ ኣቶ መለስና ኮ/ል ኢያሱ ብቻ የፈጠሩት ኣዲስ 'ታሪክ' ነው። ኣቶ መለስ በጠላት ተከቦ ኣያውቅም። በዓድዋና በዓዲዳዕሮ ሳይከበብ በጥይት ድምፅ ብቻ እንደ በግ የሚበረግግ ሰው እንዴት ቢሆን ነው በጠላት ተከቦ ጀግና የሚወጣው ? ብሎ ለሚጠይቅ ሰው መልሱ ምን ይሆን ! ከዚሁ ጋር ተያይዞ የሚነሳ ሌላ ነጥብ ኮ/ል ኢያሱ በመፅሓፉ ኣቶ መለስን እንደ 3ኛ ሰው በርቀት በማንሳት በትረካው እጅ እንደሌለበት ኣስመስሎ ለማቅረብ ብዙ ጥረዋል። እዚህ ላይ ደርሶ ግን "በመለስ ኣገላለፅ ..." ሲል ድንገት ሸልኮት ነው ወይስ መለስ ከጎኔ ኣልተለየምና ምንም ማድረግ ኣልችልም ሊለን ፈልጎ ነው ? የሆነሆኖ ፀሓፊው ኮ/ል ኢያሱ መንገሻን የምማፀነው "...ነሓሴ 21 1969 ዓ/ም ዓዲዳዕሮ... ውጊያ" ላይ ምንህ ላይ ነበር የቆሰልከው ? ማንስ ኣከመህ ? ጠባሳውስ ማየት ይቻላልን ? ብሎ መለስን በመጠየቅ <u>በመለስ ኣገላለፅ</u> መልሱ እንዲያሳውቀን ነው።

ሌላ የሚያናድድ ቅጥፈት ደግሞ የታጋይ ሸዊት መስዋእትነት በሚመለከት ነው። ሸዊት ጥልቅ ኢትዮጵያዊ ራዕይ የነበረው፣ ለዓላማውም የተሰዋ ኣስተዋይና ደፋር ታጋይ ነው። ይህ ኢትዮጵያዊ ራዕዩ ከመለስና መሰሎቹ ጋር ችግር ውስጥ እንደከተተው ለሸዊት ቅርበት የነበራቸው ታጋዮች ኣሁን ይገልፃሉ። መለስን ዋና ተጠያቂ የሚያደርገው የሸዊት ኣሟሟት ግልፅ እየሆነ እንዳይወጣ በመፅሓፉ ቢያንስ በ 3 ቦታ (ገፅ 80፣ 178፣ 192) ስለ መስዋእትነቱ በመደጋገም ኣድበስብሶ ይጠቅሰዋል። ኣጠቃቀሱ ግን ከይሲ ተንኮል (dirty trick) ቢሆንም መቼ ? የት ? ለሚሉ ጥያቄዎች ለምን ?ን ስንጨምር ሃቁ ኮለል ብሎ ይወጣል። የመስዋእትነት ድግግሞሽ ኣቀራረቡ በሸዊት ኣሟሟት የመለስ እጅ እንደሌለ ኣስመስሎ ለማቅረብ የሚደረግ ከንቱ ሙከራ ነው። በኣቶ መለስ ውሳኔ ታጋይ ሸዊት ኣጥተነዋል። ይህ ኣሳዛኝ ድርጊት ኮ/ል ኢያሱ ጭራሽ ሊያውቀው የሚችል ጉዳይ ኣይደለም። መለስ የህሊና ፀፀት ኣላስቀምጥ ካለው መፍትሄው በግልፅ ወጥቶ መናዘዝ ነው።

ከመደምደሜ በፊት ኣንድ የሚያስቅ ቅጥፈት ደግሞ ልጠቁም ፣ በገፅ 44 ነው። መለስ ወድቆ ጭንቅላቱ ድንጋይ ሊቀበው ሲል በሪሁ ህይወቱን ኣተረፈው ይላል። ይህ ታሪክ ተብሎ በፅሁፍ መቅረቡ ራሱ ኣስቂኝ ነው። ለነገሩ እንኳንና ታጋይ ተብሎ ኣብሮህ የተሰለፈ ማንም ሰውም ቢሆን ኣደጋ ላይ ሊወድቅ ሲል ከኣደጋው ማትረፉ ባህሪያዊና ሰብኣዊ ቢሆንም የተጠቀሰው ድርጊት ግን ጭራሽ ኣልተደረገም። የት ? መቼ ? ብለን ብንጠይቅ መልስ ኣይገኝለትም። መለስና ኢያሱ የት? መቼ? ለሚሉ ተጨባጭነትን ጎርጉረው ለሚያወጡ ጥያቄዎች ጀርባቸውን ሰጥተዋል። ነገሩ ግን እንዳው ተራ ውሸት ነውና ስቀን ብናልፈው ይመረጣል። ያም ሆኖ እንደዚህ ኣይነት ውሸት ለምን እንደሚያገለግል ግልፅ ባይሆንልኝም፣ መፅሓፉ በጠቅላላ በዚህ ዓይነት ውሸት የተቀነባበረ ርካሽ ስራ መሆኑ ኣሳስቤ ማለፍ እወዳለሁ። ሌሎች በኔ ላይ ያወረዱዋቸው ኣሉ-ባልታዎች እዚሁ መልስ ለመስጠት መሞከር ኣሰልቺ ስለሚሆን ሌላ ጊዜ ብመለስበት ይሻላል። ታሪክ በማስመሰል ወይም በመቀባባት ወይም በማፈን ተቀብሮ የሚኖር ኣይደለምና! በታሪክ ባለሞያዎች ሳይመረመር ወይም ሳይተችበት ታሪክ ተብሎ የሚቀርብ ፅሁፍ ሁሉ ውድቅ ማድረግ ያስፈልጋል ብዬ ኣምናለሁ። ውሎ-ኣድሮ ጎልቶ መውጣቱ ለማይቀረው ታሪክ፣ ሃቁን ከውሸቱ፣ ጭብጡን ከፈጠራው ለይተው መረጃን በማጣቀስ ልኩን የሚነግሩን የታሪክ ተመራማሪዎችና ፀሓፊዎች በወቅቱ ብቅ እንዲሉ እማፀናለሁ።

ባጠቃላይ ይህ " መለስ ዜናዊ እና የህወሓት የትግል ጉዞ " የተሰኘው መፅሓፍ ቢያንስ የኣቶ መለስ ቅንብር እንደሆነ፣ ኮ/ል እያሱ ሊደርስባቸው የማይችሉ ኣያሌ ክንዋኔዎችን በማጣቀስና የመለስ ኣራዳዊ ክርክር በመጠቆም ለማስረዳት ተሞክረዋል። በመፅሓፉ የተጠቀሱትን መረጃዎች በማሰባሰብና ረዳት ፀሓፊ በመሆን ኢያሱ ኣላገለገለም ኣይባልም።

የኣስተማሪው ኣቶ መለስ ኣራዳዊ ሙግት ተከኖታል ለማለት ግን ኮ/ል ኢያሱን ቀረብ ብሎ በመስቀለኛ ጥያቄ ማወቅን ይጠይቃል።

በዚህ የመለስ/ኢያሱ የፈጠራ ስራ ሊተላለፍ የተሞከረው፣ ኣቶ መለስ የፈፀማቸው ኣስፀያፊ ድርጊቶች ቢያንስ ተድበስብሰው፣ ኣልያም በጀግናዊና በገንቢ ስራዎች ተተክተውና እንደምንም ተሸሞንምነው ታሪክ ብሎ ለማቅረብ ነው። ሁለቱም ያልገባቸው ነገር፣ **ትልቅ ስም በትልቅ ስራ እንጂ በትልቅ ቅጥፈት ኣይገኝም**። በቅጥፈት የተጠፈጠፈ ስም ውሎ ኣድሮ መጋለጡ ኣይቀሬ ከመሆኑ ባሻገር ሌላ የተዘነጋ ነገርም ኣክሎ ብቅ ማለቱ ስለማይቀር " **ሸውራራ ብትኳል ለትዝብት**" የሚለውን ቢሂል ማጤኑ ይሻላል እላለሁ። ለኣሁኑ ብቻ ሳይሆን ለወደፊቱም!

ኣድርባዮች "መለስ ትልቅ መሪ ነው" ስላሉ የምራቸውና እውነት የሚመስለው ሰው ኣይጠፋም። ከነዚሁም ኣንዱ መለስ እራሱ ነው። ይህ ሰው ራሱን ብቻ የሁሉን ነገር ማእከል ያደረገ (egomaniac) የማይድን በሽታ የተጠናወተው፣ ስለ ሃገር ሉኣላዊነት - ስለ ህዝብ መብት መከበር ስሜት የሌለው፣ 20 ዓመት ሙሉ ደም እያፈሰሰ ገዝቶ ኣሁንም (እንደ ኪም ኤልሶንግና ኪም ዮንግ ስልጣንን ውርስ ለማድረግ) ለግምጃ ቤት ሹመኛዋ ሚስቱ ሊዳርገን እያውጠነጠነ ያለ፣ ስለ **ቅንድቡ** ሳይቀር የሚያስዘፍን ያፄ ቦካሳ ተምሳሌት

ነው። ሽንገላዎቹ ሁሉ ለግሉ ተቀብሎት በፅሁፍ ማስፈሩ ለብቻው እጅግም ባላሳሰበኝ። ትልቁ ችግር በሽንገላው ልክ የትግሉ ታሪክ ተወላግዶ መቅረቡና ያሁኑ ይሁን መጪው ትውልድ ውሸት ሲጋትና ፈጠራን እንደ እውነት ሊቀበል ሲገደድ ማየቱ ነው። እነዚህ የፈጠራ ታሪኮች በየትምህርት ቤቱ ጭምር እየተረጩ ናቸው። ኣማራጭ ደግሞ እንዳይኖር ኣድርገዋል። ህዝቡን የመቃወም መብት ኣሳጣተውታልና። እውነቱን ሊያቀርብ የሚችለው ኣማራጩ “በሕግ” ታግደዋል። ታፍነዋል። ኮ/ል ኢያሱ እንደጠቀሰው ሳይሆን ሓሳብን በነፃነት የመግለፅና የመቀበል መብት የለም። እሱ ማስረከብ በነበረበት የመንግስት ቤት ተቀምጦ ስለፃፈና በግምጃ ቤት ሹመኛዋ ወጪ የባሏ መወድስ ስለታተመ ‘የመፃፍ ነፃነት’ ኣለ ሊለን ከቶ ኣይችልም። ሓሳባቸው ለመግለፅ የፃፉ፣ የተናገሩና በሰላም የተሰለፉ ዜጎች “ሕገ-መንግስት ኣፍራሽ” “ሽብርተኛ” እየተባሉ በጠራራ ፀሓይ ሲረሸኑ፣ ወህኒ ሲወርዱ፣ ሲደበደቡና “ሲሰወሩ” ተገንዝበናል። ከኣሰፋ ማሩ ጅምሮ እስከ ኣረጋዊ ወ/ዮሃንስ የት እንደደረሱ እናውቃለን። ስለዚሁ ያለው ምርጫ የኣቶ መለስና ኣጃቢወቹ ሃበስ-ቀደስ ትረካ ብቻ ለትውልድ ማስተላለፍ ሊሆን ነው። ይህ ደግሞ ውሸትን ማስተማር ማለት ነው። ልጁ ውሸት ሲማር ሊያይ የሚፈልግ ወላጅ እንደሌለ ሁሉ ትውልድ ለዚህ ሲጋፈጥ ኣእምሮ ያለው ሰው ሁሉ ሊከነክነው ይገባል። የታሪክ ሙሁራንም፣ ታሪክ የፈጠራ ስራ ሆኖ ሲቀርብ መቃወሙ ሙያዊ ግዴታቸው መሆኑ ኣውቀው ሃላፊነታቸውን እንዲወጡ ከወዲሁ በድጋሚ በትህትና ኣሳስባለሁ።

ኣረጋዊ በርሀ
ዘ ሄግ
09/12/10

ኢትዮሚድያ - Ethiomedia
December 9, 2010